የሰበር መ/ቁ 28764

ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የወ/ሮ አመለወርቅ እየሱስ ወራሽ ጠበቃ ሰለመን ገ/መቀል ቀረቡ

ተጠሪዎቹ፡- 1. አቶ መስፍን አስፋው
2. ወ/ሮ አልማዝ አስፋው
3. ቱቱ አስፋው
4. ሶስና አስፋው

ጠበቃ መልካም ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዮ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22238 ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48910 ታህሣሥ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ጥር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ከመዝገቡ ለመረዳት እንደሚቻለው በመጀመሪያ የአሁን ተጠሪዎች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው እህታችን ወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው በ1995 ዓ.ም በሞት

ተለይታለች። እህታችን ልጅ ወይም ተወላጅ የሌላት መሆኑና እኛ ወራሾቿ መሆናችንን በፍርድ አረጋግጠናል። ሟች እህታችን ወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው ከወደ ውጭ አገር ለህክምና ስትሄድ ቤቷንና ንብረቷን ለአቶ ፈንታይ ወልደዮሐንስ እና ወ/ሮ የሺመቤት ሀብተሚካኤል ሰጥታ ሄዳለች። ሆኖም አደራ ተቀባዮች የሆኑት እነ አቶ ፋንታዬ የውርሱን ንብረት እንዲያስረክቡን ስንጠይቅ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥሩ 761 የሆነውን ቤትና በክሱ የተዘረዘሩ ንብረቶች እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል።

ተጠሪዎች የውርስ ንብረቱን ይዘዋል ከሚሏቸው ከእነ አቶ ፈንታዬ ወልደዮሐነስና ወ/ሮ የሺመቤት ሀብተሚካኤል ጋር እየተከራከሩ እያሉ ወ/ሮ አመለወርቅ እየሱስ ቀርበው ሟች ጥሩወርቅ አስፋው የሟች አቶ አበበ ከበደ ሚስት ነበሩ። እኔ የአቶ አበበ ከበደ ሚስት መሆኔን በፍርድ ቤት አረጋጋጫለሁ። ክርክር እየተካሄደበት ያለው ንብረት የሟች አበበ ከበደ የጋራ ሀብት በመሆኑ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በማለት ያመለከተች ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአመልካችን ማመልከቻ እና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ወደ ክርክሩ በጣልቃ ገብነት እንድትገባ ወስኗል።

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ክስ የአመልካች አውራሽ የሆነችው አመለወርቅ እየሱስ በጣልቃ ገብነት ያቀረበችውን ማስረጃና የእነ ፈንታዬ ወልደዮሐንስን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ‹‹ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ 1ኛ ተጠሪ ያልካዱና ክሱን ስለአመኑ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 242 መሠረት በዝርዝር የተያዘው ንብረት በራሱ ላይ ተዘርዝሮ የቀረበው ንብረት ለአመልካቾችና ለጣልቃ ገብ እንዲያስረክቡ። ሁለተኛ ተጠሪ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ሲሆን ባለቤታቸው ለህክምና ወደ ውጭ እንደሄዱና ሲመለሱ እንደሚፈጽሙ በመግለጽ ለጊዜው ከነገር ለመሸሽ እኔ ንብረቱን አልተረከብኩም በዝርዝር ላይም አልፈረምኩም ይበሉ እንጂ ክሱን

በግልበጽ ስላልካዱ በነገሩ የመሸሽ የተሰጠ መልስ ክሱን እንደመካድ ስለማያስቆጥር ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ አንደኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ሀላፊ ናቸው ብለን ወስነናል። ጣልቃ ገብም ተካፋይ ናቸው ብለናል።›› በማለት ወስኗል። የፌዴራልና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከክሱ ጋር በዝርዝር የተያዘው ንብረት በክሱ ላይ የተመለከተው ወይም የሟች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍሉን እንዲያስፈጽሙ አቶ ቸርነት ተገኝን ሹሟል።

ከዚህ በኋላ ውርስ አጣሪው በተጠሪዎችና አመልካች የግልና የሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በሚሉት ጉዳይ ላይ ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 በተደነገገው መሠረት መብታቸውን ያልጠየቁ ስለሆነና በአዲስ አበባ አስተዳደር በየካ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 02 ቁጥሩ 761 የሆነው ቤት ወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው የተመዘገበ ስለሆነ የእሷ የግል ንብረት የሚልና ሌሎች ንብረቶችም ወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው የግል ሀብት ናቸው በማለት ወስኖ ይህንን ሪፖርት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቧል። ፍርድ ቤቱም የውርስ አጣሪው ሰኔ 25 ቀን 1998 ከተፃፈ መሸኛ ጋር የቀረበለትን ሪፖርት ህግና ሞራልን የማይቃረን በመሆኑና ተከራካሪዎቹ ትክክለኛነቱን ቀርበው ስላረጋገጡ የፍርድ ቤቱ የውሣኔ አካል አድርጐ መዝግቦታል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ወሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርባ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል። አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማጽደቅ የሰጠውና ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረብኩትን ይግባኝ ለመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቱ የሾማቸው የውርስ አጣሪ ከእኛ በኩል ያቀረበውን ማስረጃ ተቀብለው አልመረመሩም። ፍርድ ቤቱ የውርስ ከጣሪው ባቀረበው ሪፖርት ላይ በጽሑፍ

መቃወሚያ ብይን ሣይሰጥ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ማጽደቅ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ከሁሉም በላይ በጣልቃ ገብ ተከራካሪነት ቀርበን ባቀረብነው ክስና ማስረጃ መሠረት በክርክር የተያዘው ሀብት የወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋውና የአቶ አበበ ከበደ የጋራ ንብረት እንደሆነ በማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ንብረቱን በአደራ የያዙትና በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩት እነ ፈንታዬ ወ/ዮሐንስ ንብረቱን ለከሳሾች (ተጠሪዎች) እና ለጣልቃ ገብ ያስረክቡ ጣልቃ ገብ ተከፋይ ናቸው በማለት ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ የውርስ አጣሪው ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በማከራከር ውሣኔ መስጠቱና ፍርድ ቤቱም ተቀብሎ ማጽደቁ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል ተጠሪዎች በበኩላቸው የባልና የሚስቱ ግንኙነት ከተቋረጠ ሰላሣ አመት የሆነው በመሆኑ አቶ አበበ ከበደ ከዚህ በፊት የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠባቸው በመሆኑ የውርስ አጣሪው ንብረቱ የግል ነው ወይስ የጋራ የሚለውን አጣርቶ እንዲወሰን የተሾው በመሆኑና ይህንንም ያደረገው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ስልጣን መሠረት በመሆኑ በአጠቃላይ በውርስ አጣሪውም ሆነ በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ሀምሌ 13 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ሟች አበበ ከበደ በህይወት አለመኖራቸው የተረጋገጠው 1984 ዓ.ም በመሆኑ ከዚህ ጊዜ በፊት የተፈራው ሀብት የጋራ ሀብት ነው፡፡ የቤቱ ፕላንና ሥራው የተፈቀደው ከአቶ አበበ ከበደ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ሌሎች ንብረቶች መኪና፣ በባንክ የተያዘው ገንዘብ እና ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች የጋራ ሀብት ናቸው የውርስ አጣሪው ከማጣራት ተግባር ወጥተው ህግ የመተርጐም ሥራ የሠሩ በመሆናቸውና ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ተቀብሎ የፀደቀ በመሆኑ

መሠረታዊ የህግ ስህተት በሥር ፍርድ ቤቶች በኩል ተሰርቷል በማለት የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ በኩል የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው፡፡

1ኛ ተጠሪዎች የሟች የወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው ንብረት ነው በማለት ዘርዝረው በእነ አቶ ፈንታዬ ወልደዮሐንስ ላይ ክስ አቅርበው ሲከራከሩበት የነበረው ንብረት የአመልካች አውራሽ የአቶ አበበ ከበደ የጋራ ሀብት መሆኑ በፍርድ ተወስኗል ወይስ አልተወሰነም?

2ኛ የፌዴራል የመጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሾመው የውርስ አጣሪ የውርስ ማጣራቱን ተግባር ያከናወነው በተሰጠው የስልጣን ወሰን ሣያልፍና በህግ መሠረት ነው ወይስ አይደለም ለሚሉትን ጭብጦች እልባት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በክርክሩ እንድትገባ ጥያቄ ያቀረችው ተጠሪዎች አይነቱን መጠኑንና ዋጋውን ዘርዝረው ክስ አቅርበው የሚከራከሩበት ንብረት ያአውራሽ የጋራ ሀብት መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ ተጠሪዎች ክስ ያቀረብንበት ንብረት የአመልካች አውራሽ አቶ አበበ ከበደ የጋራ ሀብት አይደለም ስለዚህ በክርክሩ ጣልቃ የምትገባበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን ጣልቃ ገብነት በመቃወም ያልተከራከሩ መሆኑን በአንፃሩ የጣልቃ ገቧን አቤቱታ በተመለከተ ንብረት በሚጣራበት ጊዜ የሚታይ በመሆኑ ለጣልቃ ገብ አቤቱታ መልስ መስጠት ሣያስፈልገን ይወሰንልን በማለት ምላሽ እንዲሰጡ የፌዴራል የመጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 23 ቀን 1997 ዓ.ም ከሰጠው ብይን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪዎች የአመልካችን በጣልቃገብነት ያቀረበችው ክርክር ላይ አለን የሚሉትን ክርክርና ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በንብረት ማጣራት ሒደቱ እንደሚታይ ያሣሰቡ ቢሆንም

ፍርድ ቤቱ ይህንን ጥያቄቸውን በመቀበል በግልጽ ብይን አልሰጠም ፍርድ ቤቱ መጋቢት 23 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በሥር ፍርድ ቤቱ በተከሳሽነት የሚከራከሩ ሰዎች ንብረቱን ለተጠሪዎችና (ከሳሾች) ለአመልካች ለሥር ለጣልቃ ገብ ያስረክቡ፡፡ ጣልቃ ገብ ተካፋይ ናቸው በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ክርክር የቀረበበት ንብረት የአውራሻችን የጋራ ሀብት ስለሆነ ግማሹ ይገባኛል በማለት አመልካች ያቀረበችውን ማመልከቻና ማስረጃ በመቀበል በመዝገቡ ክርክር እየተደረገበት ያለው ንብረት የሟች አበበ ከበደ የጋራ ሀብት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች በእነ ፋንታዬ ወ/ዮሐንስ አላግባብ ስለያዙ እንዲያስረክቡን በማለት በክስ ማመልከቻቸው ላይ የዘረዘሩት ንብረት የሟች ወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋው የግል ንብረት ብቻ እንዳልሆነና ክርክሩ እየተካሄደበት ያለው ንብረት የአመልካች አውራሽ የአቶ አበበ ከበደ የጋራ ንብረት መሆኑ ከንብረቱም አመልካች ተካፋይ እንደሆነች ፍርድ ቤቱ ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ በውርስ አጣሪም ሆነ በሌላ አካል እንደገና ክርክርና ማስረጃ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ተጠሪዎች ለውርስ አጣሪው ያቀረቡት የህግ እና የፍሬ ጉዳይ ክርክር የፍታብሔር ሥነ ሥርህት ሕግ አንቀጽና ድንጋጌ የሚጥስና መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 23 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በፍርድ የቋጨውን ጉዳይ እንደገና አይቶ አከራክሮ የውርስ አጣሪው ያቀረበውን የውሣኔ ሀሳብ ተቀብሎ ማጽደቁና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ስህተቱን ሣያርም የአመልካችን ይግባኝ መሠረዙ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪውን የሾመው የወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋውን የውርስ ንብረት አጣርቶ እንዲቀርብ መሆኑ በውሣኔው

ተቀምጧል፡፡ የውርስ አጣሪ ስልጣንና ሀላፊነት በፍታብሔር ህግ የውርስ ድንጋጌዎች በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 956 የውርስ አጣሪው ሥራ፡-

- ሟች አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻው ውርስ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ
- የውርሱን ሀብት ማስተዳደር
- መክፈያቸው የደረሰውን የሟች ዕዳዎች መክፈል
- ሟች በኑዛዜ ያደረጋቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለማስፈፀም ማንኛውንም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ እንደሆነ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ የውርስ አጣሪው ሥራውን ማከናወን ያለበት ይህንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሾመው ውርስ አጣሪ በህግና በፍርድ ቤቱ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በፍርድ የተቋጨውን ጭብጥ ላይ የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በክሱ ከተዘረዘሩት ንብረቶች ውስጥ የሟች ወ/ሮ ጥሩወርቅ አስፋውና የሟች አበበ ከበደ በጋብቻ ያፈሩት የጋራና የግል ንብረት አስመልክቶ ያቀረበው የውሣኔ ሀሳብ ውርስ አጣሪው ከስልጣኑ ውጭ የሠራውና ወዲያውኑ ፍርድ ቤቱ ሊሰርዘው የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ውርስ አጣሪው የባልና የሚስት የጋራ ሀብት የሚመለከቱ የህግ ድንጋጌዎች በመተርጐም ተጠሪዎች የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ስለሚታገድ ጣልቃ መግባት የለባትም በማለት ለፍርድ ቤቱ ያላቀረቡትን ክርክር በውርስ ማጣራት ሒደት የይርጋ ክርክር አንስተው ሲከራከሩ የይርጋ ክርክሩን በመቀበልና በአቶ አበበ ከበደ ስም ተመዝግባ የምትገኘዋን ኮድ 2-17736 ፒክአፕ መኪናና እና ሌሎች ንብረቶች ከአመልካች በአስራ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልጠየቀች በመሆኑ

አሁን ልትጠይቅ አትችልም የሚል የውሣኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለፍርድ ቤት ያቀረበ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ውርስ አጣሪው ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የባልና ሚስቱን የጋራና የግል ሀብት ለመወሰን ያቀረበውን የህግ ክርክር አስመልክቶ የሰጠው የህግ ትርጓሜና የማስረጃ ተቀባይነት የማስረጃ ክብደትና የማስረጃ ታማኝነት አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሳይመረምር የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ማጽደቁና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ጉልህ ስህተት ማለፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና አመልካች መብቷን በዳኝነት ስልጣን በሌላው ግለሰብ ከስልጣኑና ሀላፊነቱ ውጭ በሠራው ሥራ መነሻ እንዲታጣ ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው በዚህ ጉዳይ የውርስ አጣሪ ሆኖ የተሾመው ሰው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 956 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ክስ ውርስ አጣሪ ስልጣንና ሀላፊነት እንደዚሁም የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ስለ ምትክ ዳኛ ስልጣንና ሀላፊነት ከተደነገጉት ድንጋጌዎነች ውጭና ፍርድ ቤቱም የሰጠውን ስልጣንና ሀላፊነት ለመተላለፍ የይርጋ የህግ ድንጋጌዎች የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎችንና የንብረት ህግ ድንጋጌዎች ተገቢ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ሥራውን ያከናወነ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አጣሪው ከተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት ውጭ በህግ ጉዳዮች በማከራከርና የህግ ትርጓሜ በመስጠት ያቀረበውን የውሣኔ ሀሳብ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም ብሎ እንዳለ ተቀብሎ ማጽደቁ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና የዳኝነት አካሄድ በሂደቱ ላይ ጉለት መፈፀሙን የሚያሣይ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በተገለፀው ምክንያት የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪውን የውሣኔ ሀሳብ በማጽደቅ የሰጠው ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ

ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በማጽደቅ የሰጠው ትእዛዝ መሠታዊ የህግ ስህተት አለት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22238 ሀምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ሙሉ በሙሉ ለማጸደቅ የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48910 ታህሣሥ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪዎች በፌዴራል የመጀመያ ፍርድ ቤት እነ ፈንታዬ ወልደዮሐንስ ያስረክቡን በማለት የጠቀሱት በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥር 761 የሆነው ቤት በአቶ አበበ ከበደ ስም ተመዝግባ የምትገኘው መኪና፣ በባንክ ቤት የሚገኝ ገንዘብና በአደራ ማስቀመጫ የተቀመጠ ጌጣጌጥ እንደዚሁም ሌሎች የቤት ቁሣቁሶችና ንብረቶች የሟች አበበ ከበደ የጋራ ሀብት መሆናቸውን መጋቢት 23 ቀን 1997 ዓ.ም በፍርድ የተወሰነ በመሆኑ ግማሹን ለአመልካች ማካፈል አለባቸው በማለት ወስነናል፡፡ በፍርዱ መሠረት እንዲያስፈጽም ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ